በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Revenues
የውስጥ ማስታወሻ
INTERNAL MEMO

ለ፡- ለኮምኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ከ፡- ታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት
ቀን፡- 20/11/2014 ዓ.ም

አባይነሽ አባተ
የታክስ ማስታወቅ
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

**ጉዳዩ፡- የእንስሳት መኖ ግብዓቶችን ታክስን ይመለከታል፡፡**

የእንስሳት መኖ ለማምረት የሚያገለግሉ ግብዓቶች ከውጪ ሲገቡም ሆነ ከሀገር ውስጥ ግዥ ሲፈፀምባቸው ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ መሆናቸውን ገንዘብ ሚኒስቴር መጋቢት 26/2014 ዓ.ም በቁጥር ማኢ..30/7/5279 ለጉምሩክ ኮሚሽን የተፃፈ ደብዳቤ በመጥቀስ የጉምሩክ ቀረጥ ማሻሻያ ግብዓቶች ለግብርና አላማ መምጣታቸው በግብርና ሚኒስቴር ማረጋገጫ እየተሰጠባቸውና ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገባቸው ከቀረጥና ታክስ ነፃ መደረጋቸውን ሰኔ 21/2014 ዓ.ም በቁጥር ማኢ..30/7/5698 በተፃፈ ደብዳቤ አሳውቆናል፡፡

---

ይሁንና ለታክሱ አስተዳደርና አፈፃፀም ያመች ዘንድ ታክሱን ከፍለው በተመላሽ ስርዓት እንዲስተናገዱ እንዲደረግ ለአፈፃፀም የተላለፈ ስለሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸውና በዘርፉ የተሰማሩ የእንስሳት መኖ አምራችና ሻጭ ድርጅቶች እንዲያውቁትና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ዝርዝር አፈፃፀሙን በተቋሙ ድረ ገፅ ( ዌብ ሳይት) በቋሚነት እንዲጫን ፤እያሳወቅን የሚጫነውን ውሳኔ የተላለፈበትን ደብዳቤ 5 ገፅ ኮፒ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር//

ግልባጭ፡-

- ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ
  ገቢዎች ሚኒስቴር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር ____________

Ref.No

ቀን ____________

Date

| ተ.ቁ | ታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| | | ማሽነሪዎች ጭምር/<br>Other packing or wrapping machinery (including heat- shrink wrapping machinery) |

19. ከመ/ቤታችን ሚያዚያ 01 ቀን 2013 ዓ.ም በቁጥር 6.3/0176/13 በተጻፈ ደብዳቤ ታሪፍ ቁጥር 1806.2010 "--- በበልክ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚመጣ ቸኮላት" ተብሎ የተላለፈው ከሚያዚያ 01 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ይህ የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ማሻሻያ ይህ ደብዳቤ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ከአምስት የሥራ ቀናት በኋላ ተቀባይነት በሚያገኙ የጉምሩክ ዲክላራሲዮኖች ላይ ተግባራዊ እንዲደረግ የተወሰነ ሲሆን፣ የትራንስፎርመር አምራቾች ያስመጧቸው ጥሬ ዕቃዎችን በሚመለከት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈለባቸው በእንጥልጥል ላይ ያሉ ጉዳዮች በዚሁ መሠረት ተፈጻሚ እንዲደረጉ እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

* የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * ገንዘብ ሚኒስቴር 6

(እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፡-

- ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
  ገንዘብ ሚኒስቴር
- ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
  አዲስ አበባ

የገንዘብ * የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 6 * ሚኒስቴር